በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

ትምህርት ቢሮ

የተማሪ መማሪያ መጽኃፍና የመምህር መምሪያ ለመገምገም የተዘጋጀ መስፈርት

የመጽሃፍ ገምጋሚዎች መምህራን መረጣ የሚከናወነው በአዲሱ ስርዐተ ትምህርት የሙከራ ትግበራ ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን ብቻ ሲሆኑ ከዚህ በታች የተቀመጠውን የምልመላ መስፈርት ሊያሟሉ ይገባል፡፡

- በሚገመገመው መማሪያ እና ማስተማሪያ መጽኃፍት የትምህርት አይነትና ክፍል ደረጃ በማስተማር ላይ የሚገኙ፤
- በሚገመገመው የትምህርት አይነት የመጀመሪያ ዲግሪ እና በላይ የትምህርት ዝግጅት ያላቸው፤
- የአገልግሎት ዘመናቸው በመምህርነት ሙያ ዘርፍ 5 አመት እና በላይ አገልግሎት ያላቸው፤
- የተሻለ የስራ አፈጻጸም/ የሶስት ሴሚስተር አማካኝ / ያላቸው
- በሙከራ ትግበራ በዋለው ትምህርት የትምህርት ይዘቱን በጥልቀት የተረዱ፤
- የተለያዩ የምዘና ዘዴዎችን በመረዳት ተግባራዊ ያደረጉ፤
- የከተማውን ነባራዊ ሁኔታ በአግባቡ የተረዱ፤
- የማስተማር ስነዘዴን በአግባቡ ተረድቶ ስራ ላይ ያዋሉ፤
- በመምህርነት ሙያዊ ስነምግባር አርዓያ የሆኑ
- በመማር ማስተማሩ ዙሪያ ተግባራዊ ጥናትና ምርምር በማድረግ እውቅና የተሰጣቸው፤ጥናቱን ማቅረብ የሚችሉ
- አዲሱን ስርዓተ ትምህርት የተገመገሙ እና ከስርዓተ ትምህርት ኮሚቴ ማረጋገጫ የተሰጣቸው፤

ማሳሰቢያ፡-

1. በመጽኃፍ ዝግጅት ላይ የተሳተፉት አዘጋጆች ስለሆኑ በግምገማ ምልመላ ውስጥ ተሳታፊ መሆን አይችሉም፡፡
2. ምልመላው የሚከናወነው በሙከራ ትግበራ ትምህርት ቤቶች ላይ ብቻ ነው፡፡